# KNOW THE GLOW®




የአይን ውስጥ ፍካት በአይን ውስጥ የሚታይ ጤናማ ያልሆነ ምልክት ሲሆን በርካታ መታከም የሚችሉ የአይን ህመሞችን ሊያመላክት ይችላል።

የአይን ውስጥ ፍካት በቀላሉ በምናነሳቸው ፎቶዎች ላይ ሊታይ ስለሚችል ወላጆች /አሳዳጊዎች በቶሎ የህክምና እርዳታ በመፈለግ የልጆቻቸውን እይታ አንዳንድ ጊዜም ህይወት እንዲታደጉ ያስችላቸዋል።

## ራዕይ

መታከም ወይም መከላከል የሚቻሉ የልጅነት አይነስውርነትን የሚያመጡ ህመሞችን ወይም እክሎችን ከአለም ላይ ማጥፋት።

## አላማ

የህክምና እና አጠቃላይ ማህበረሰብን ስለ “የአይን ውስጥ ፍካት” በማስተማር የልጅነት አይነስውርነትን መከላከል።

## (ስለ “እይን ውስጥ ፍካት” መረጃዎች)

- እድሜያቸው እስከ 9 ዓመት በሆኑ ህፃናት ላይ ከ80 ህፃናት አንዱ የዓይን ውስጥ ፍካቱን ያሳያሉ።
- ከ 80 በመቶ በላይ የሚሆነው የብርሀን መቀበያ ክፍል ካንሰር (ሬቲኖብላስቶማ) እና በተፈጥሮ የሚከሰት የብርሀን መቀበያ ክፍል የደም ሰሮች ችግር (ኮትስ በሽታ) በመጀመሪያ በወላጅ ወይም በቤተሰብ አባል አማካኝነት በአይን ውስጥ በሚታይ ፍካት ምክንያት ይታወቃሉ፡
- የአይን ውስጥ ንጣት (ፍካት) ከ 30 በላይ የእይታ እክሎች እና በሽታዎች፤ ሬቲኖብላስቶማን ጨምሮ ፤ አመላካች ሊሆን ይችላል።

KNOW THE GLOW®

# (ስለ ዓይነ -ሰው ርነት መረጃዎች)

- በአለም ውስጥ አንድ ልጅ በየ60 ሰከንድ ዓይነ-ሰውር ይሆናል።
- በየዓመቱ ወደ ግማሽ ሚሊዮን የሚጠጉ ሕፃናት ለዓይነ-ሰውርነት ይዳረጋሉ።
- ዓይነ-ሰውርነትን የመከላከል ጥረቶች ካልተጠናከሩ  የዓይነ-ሰውራን ቁጥር በ 2050 በሦስት እጥፍ ይጨምራል።
- 80% የሚሆነውን የህፃናት የአይነ ሰውርነት ምክንያት መከላከል ወይም ማከም ይቻላል።
- በዓለም ዙሪያ 39 ሚሊዮን ሰዎች ዓይነ-ሰውራን ናቸው።
- በአለም አቀፍ ደረጃ 285 ሚሊዮን ሰዎች የእይታ  ግድፈት ያለባቸው ናቸው።



## ልጆችዎን ፎቶ ያንሱ። የአይን ውስጥ “ፍካቱ ” በዓይናቸው ምስል ውስጥ ከተገኘ ልጆችዎን ወደ ህክምና ቦታ ወሰደው ያስመርምሩ።

የአይን ውስጥ “ፍካቱ” በብርሃን የተነሱ ፎቶዎች ላይ በአይን ውስጥ  ነጭ፣ ግልጽ ያልሆነ ወይም ቢጫ ሆኖ ይታያል፣ ይህም ከ30 በላይ የሚሆኑ የተለያዩ የአይን ህመሞችን  እና ሁኔታዎችን ሊያመላክት ይችላል።

### (ወላጆችን የምንጠይቃቸው/የምናሳስባቸው:-

1. የቆዩ ፎቶዎችን በማየት ወይም ልጅዎን አዲስ ፎቶዎች በማንሳት “የአይን ውስጥ ፍካቱን” ይፈልጉ።
2. ልጆችዎ ካሜራውን በቀጥታ ሲመለከቱ የሚያሳዩትን ፎቶዎች ይገምግሙ፣ “የአይን ውስጥ ፍካቱ”  ከዚህ አቅጣጫ ብቻ ሊታይ ይችላል።
3. በስልክዎ ላይ ያለውን “የቀይ ዓይን ቅነሳ ባህሪ” ማጥፋት የልጅዎን አይን ብሩህነት ለማየት ይረዳዎታል።
4. “የአይን ውስጥ ፍካቱን” አንድ ጊዜ ሲያዩት ንቁ ይሁኑ፣ ሁለት ጊዜ ሲያዩት እርምጃ ይውሰዱ!
5. “የአይን ውስጥ ፍካቱን”   ካዩ አቅራቢያዎ ወደሚገኘው የዓይን ህክምና ማእከል በመሄድ ልጅዎን ያስመርምሩ።
6. የልጅዎን “የአይን ውስጥ ፍካቱን”  የሚያሳዩ ፎቶዎችን ወደ የዓይን ሐኪም ቀጠሮ ሲመጡ  ይዘዋቸው ይምጡ።
7. በተለይ ለትናንሽ ልጆች ወላጆች መረጃውን ለማዳረስ ይርዱን!!!

## ማንም ልጅ በማይታወቅ የዓይን ሕመም ምክንያት እይታውን ማጣት የለበትም!

ስለ “የአይን ውስጥ ፍካት”  የበለጠ መረጃ ለማግኘት www.knowtheglow.orgን ይጎብኙ።

Sources: 10 FACTS ABOUT BLINDNESS AND VISUAL IMPAIRMENT. http://www.salute.gov.it/imgs/C_17_pubblicazioni_1656_ulterioriallegati_ulterioreallegato_0_alleg.pdf. 10 little-known facts about blindness. (2015, September 24). https://www.perkins.org/stories/10-little-known-facts-about-blindness.April 2010 Issue. https://retinatoday.com/issues/2010-apr. Balmer, A., & Munier, F. (2007, December). Differential diagnosis of leukocoria and strabismus, first presenting signs of retinoblastoma. https://www.ncbi.nlm.nih.gov/pmc/articles/PMC2704541/. The Economic Burden of Vision Loss and Eye Disorders in the United States. https://www.norc.org/Research/Projects/Pages/the-economic-burden-of-vision-loss-and-eye-disorders-in-the-united-states.aspx. Global Blindness Projected to Triple by 2050. (2018, May 18). https://www.seeintl.org/global-blindness-2050/. Hollows, F. (2017, April 21). The five facts about childhood blindness you need to know. https://medium.com/@FredHollows/the-five-facts-about-childhood-blindness-you-need-to-know-eb8149eccee.Hollows, F. (2017, April 21). The five facts about childhood blindness you need to know. https://medium.com/@FredHollows/the-five-facts-about-childhood-blindness-you-need-to-know-eb8149eccee. Munson, M. C., Plewman, D. L., Baumer, K. M., Henning, R., Zahler, C. T., Kietzman, A. T., ... Shaw, B. F. (2019, October 2). Autonomous early detection of eye disease in childhood photographs. https://www.ncbi.nlm.nih.gov/pmc/articles/PMC6774731/. Myers, C. (2016, November 9). High Rate of Unemployment for the Blind. https://work.chron.com/high-rate-unemployment-blind-14312.html. Potential disease detection using photographs in childhood vision screenings. (2016, February 17). https://knowtheglow.org/research-efforts-focus-on-increased-glow-detection-through-vision-screening/. Visual impairment, blindness cases in U.S. expected to double by 2050. https://www.nei.nih.gov/about/news-and-events/news/visual-impairment-blindness-cases-us-expected-double-2050.